ቀን - / /2015 ዓ.ም.

ጋብቻን በስምምነት ለማፍረስ የተደረገ የስምምነት ውል

የጋብቻ ውል አፍራሾች ..... 1/ አቶ

2/ወ/ሮ

አድራሻ/ የሁለቱም/ :- አ/አ የካ ክ/ከተማ ወረዳ 01 የቤ/ቁጥር አዲስ

1ኛ ተስማሚ ወገን ከ2ኛ ወገን ተስማሚ ጋር በአዲስ አበባ ከተማ መጋቢት 24 ቀን 1996 ዓ.ም. ጀምሮ በክብር መዝገብ ሹም ፊት ጋብቻ ፈጽመን ይህን ፍቺ ለማድረግ እስከተስማማንበት እለት ድረስ አብረን ኖረናል፣ ሰማቸው 1.____የተባሉ ልጆችን በጋራ አፍርተናል፣ በጋራ ቤትና መኪና አፍርተናል ፣ እነዚህ ንብረቶችን ለልጆቻችን መልካም አስተዳደግ ሲባል በጋራ ለማስተዳደር ተስማምተናል ፣ የልጆቻችንን አስተዳደግ በተመለከተ ሁለተኛ ተስማሚ እናታቸው ከ18 አመት በታች ለሆኑት ከተ.ቁ. 2-4 ላሉት ልጆች ሞግዚትና አስተዳዳሪ እንዲሆኑ የተስማማን ሲሆን 1ኛ ተስማሚ በወር ብር 10000.00 /አስር ሺ/ ከጋራ ንብረታችን ከሚገኘው ገቢ ቀለብ ለመቁረጥ ተስማምቻለሁ። በሳምንት ሁለት ቀናት የመጎብኘትና ወስደው የማዝናናት መብተምና ግዴታ ላይም ተስማምተናል ። ተስማሚዎች ይህንኑ ጋብቻ በፍቺ ለመጨረስ ባለኝ ሥልጣን መሠረት ሁለታችንም ተጋቢዎች ለመለያየት የተስማማን ስለሆነ 1ኛ ወገን ተስማሚ ፍቺውን የደገፍኩ እና ከዚህ በኋላ ከጋራ ንብረትምና ከልጆቻችን አስተዳደግ ውጪ በሌላ ጉዳይም ሆነ ጥቅም ምንም ግንኙነት የሌለን ስለሆነ ጋብቻውን ያፈረስኩ መሆኔን በፊርማዬ አረጋግጫለሁ።

እኔም በ2ኛ ወገን ተስማሚ ከዚህ በላይ በተጻፈው መሠት ከ1ኛ ወገን ተስማሚ ጋር የነበረንን ጋብቻ ከዚህ በላ ለማፍረስና ለመፋታት ስለተስማማን እኔም ይህንኑ የጋብዝ ፍቺ የደገፍኩና ጋብቻውን ያፈረስኩ መሆኔን በአንድ ላይ ከባለቤቴ ጋር ሆነን በሚስትነት ከመጋቢት 24 ቀን 1996 ዓ.ም. ጀምሮ በክብር መዝገብ ሹም ፊት ጋብቻ ፈጽመን ይህን ፍቺ ለማድረግ እስከተስማማንበት እለት ድረስ አብረን ኖረናል፣ ሰማቸው____ የተባሉ ልጆችን በጋራ አፍርተናል፣ በጋራ ቤትና መኪና አፍርተናል ፣ እነዚህ ንብረቶችን ለልጆቻችን መልካም አስተዳደግ ሲባል በጋራ ለማስተዳደር ተስማምተናል ፣ የልጆቻችንን አስተዳደግ በተመለከተ ሁለተኛ ተስማሚ ከ18 አመት በታች ለሆኑት ከተ.ቁ. 2-4 ላሉት ልጆች ሞግዚትና አስተዳዳሪ ለመሆን የተስማማሁ ሲሆን 1ኛ ተስማሚ በወር ብር 10000.00 /አስር ሺ/ ከጋራ ንብረታችን ከሚገኘው ገቢ ቀለብ ቆርጠው ሊሰጡኝ ተስማምተዋል። በሳምንት ሁለት ቀናት የመጎብኘትና ወስደው የማዝናናት መብተምና ግዴታ ላይም ተስማምተናል ከዚህ በኋላ ከጋራ ንብረትምና ከልጆቻችን አስተዳደግ ውጪ በሌላ ጉዳይም ሆነ ጥቅም ምንም ግንኙነት የሌለን ስለሆነ ጋብቻውን ያፈረስኩ መሆኔን በፊርማዬ አረጋግጫለሁ።

ይህ የፍቺ የስምምነት በስምምነት የጋብቻ ውል አፍራሾች መካከል በተሻሻለው የቤተሰብ ሕግ አዋጅ ቁጥር 213/92 አንቀጽ 77 በተመለተው መሠረት የፀና ይሆናል ።

ይህ የፍቺ ስምምነት በ3 ኮፒ ተጽፎ በተስማሚዎችና በሌላም በሚመለከተው ክፍል ይገኛል ።

በወቅቱ የነበሩ ምሥክሮች

1/ ወ/ሮ

2/ አቶ __፣፣ ናቸው።

እኛም ምስክሮች የጋብቻ ውል አፍራሾች ስምምነቱ በፈቃዳቸውና በፍላጐታቸው ሲያደርጉና ይህንን የፍቺ ዋል ሲፈራረሙ አይተን በምስክርነት ፈርመናል ።

የፍቺው ተስማሚዎች ፊርማ

1/----------

2/----------

የምስክሮች ፊርማ

1/----------

2/----------

ቀን 2014 ዓ.ም

ለፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት

ከ/ቀራንዮ ምድብ ቤተሰብ ችሎት

<u>አዲስ አበባ</u>

አመልካቾች፡- ..... 1/ አቶ

2/ወ/ሮ

አድራሻ/ የሁለቱም/ :- አ/አ የካ ክ/ከተማ ወረዳ 01 የቤ/ቁጥር አዲስ

ተጠሪ፡- የለም

<u>በተሻሻለው የቤተሰብ ሕግ አንቀፅ 77(1) መሠረት በስምምነት ለመፋታት የቀረበ አቤቱታ ነው።</u>

ሀ. ፍ/ቤቱ ጉዳዩን አይቶ የመወሰን ስልጣን አለው።

ለ. አመልካቾች ጉዳዩን የምንከታተለው በራሳችን እና በጠበቃ ነው።

ሐ. ማመልከቻው በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 222 እና 223 መሠረት ተሟልቶ የቀረበ ነው።

የአቤቱታው ዝርዝር በአጭሩ

ሀ. ተስማሚ ወገን ከ2ኛ ወገን ተስማሚ ጋር በአዲስ አበባ ከተማ መጋቢት 24 ቀን 1996 ዓ.ም. ጀምሮ በክብር መዝገብ ሹም ፊት ጋብቻ ፈጽመን ይህን ፍቺ ለማድረግ እስከተስማማንበት እለት ድረስ አብረን ኖረናል፣ ሰማቸው 1. 2. 3. 4. 5. የተባሉ ልጆችን በጋራ አፍርተናል፣ በጋራ ቤትና መኪና አፍርተናል ፣ እነዚህ ንብረቶችን ለልጆቻችን መልካም አስተዳደግ ሲባል በጋራ ለማስተዳደር ተስማምተናል። እነዚህ ንብረቶችን ለልጆቻችን መልካም አስተዳደግ ሲባል በጋራ ለማስተዳደር ተስማምተናል ፣ የልጆቻችንን አስተዳደግ በተመለከተ ሁለተኛ ተስማሚ ከ18 አመት በታች ለሆኑት ከተ.ቁ. 2-4 ላሉት ልጆች ሞግዚትና አስተዳዳሪ ለመሆን የተስማማሁ ሲሆን 1ኛ ተስማሚ በወር ብር 10000.00 /አስር ሺ/ ከጋራ ንብረታችን ከሚገኘው ገቢ ቀለብ ቆርጠው ሊሰጡኝ ተስማምተዋል። በሳምንት ሁለት ቀናት የመንብኘት ወስደው የማዘናናት መብተምና ግዴታ ላይም ተስማምተናል።

ለ. ካሁን በኋላ ግን አመልካቾች አብረን መኖር ስላልፈለግን በፍቺ ለመለያየት ተስማምተናል።

አመልካቾች ከተከበረው ፍ/ቤት የምንጠይቀው ዳኝነት

በአመልካቾች መካከል ያለው ጋብቻ በፍቺ እንዲፈርስልን እንዲወሰንልን በትህትና እንጠይቃለን።

ከላይ የቀረበው እውነት ስለመሆኑ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 92 መሠረት እናረጋግጣለን።

ስለ አመልካቾች

ቀን 2014 ዓ.ም

ለፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት

ኮ/ቀራንዮ ምድብ ቤተሰብ ችሎት

አዲስ አበባ

አመልካቾች፡- ..... 1/ አቶ ፍቃዱ አሰፋ አበራ

2/ወ/ሮ ቆንጂት ነጋሽ ገብሬ

አድራሻ/ የሁለቱም/ :- አ/አ የካ ክ/ከተማ ወረዳ 01 የቤ/ቁጥር አዲስ

ተጠሪ፡- የለም

በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 223 መሠረት የቀረበ የማስረጃ ዝርዝር

የሰነድ ማስረጃ

1. መጋቢት 11 ቀን _____ ዓ.ም.በውል አዋዋይ ፊት የተደረገ የጋብቻ ሰርተፍኬት 1 ኮፒ ዋናው በእጃችን የሚገኝ፣
2. ሰኔ ቀን ዓ.ም የተደረገ የፍቺ ውል ስምምነት ገጽ ኮፒ ዋናው በእጃችን የሚገኝ፣

የሰው ምስክር

ምሥክሮች

1/ ወ/ሮ **አድራሻ :-** ቦሌ _____ **የቤ/ቁ. አዲስ**

2/ አቶ ቴ_,,,, **አድራሻ :-** **ክ/ከተማ ወረዳ የቤ/ቁ. አዲስ**

ጭብጡ ካልተለወጠ ወይም ፍ/ቤቱ ካላዘዘ በቀር አመልካቾች ያለን ማስረጃ ከላይ የተገለፀው ነው።

ስለ አመልካቾች